# የአማራጭ ኃይል መቋቋምን በተመለከተ

ጁን 2 2015 ዓ.ም

የተከበሩ ዶር ታዬ ዘገየ የሸንጎ ሊቀመንበር
የተከበሩ አቶ ሌንጮ ለታ የኦሮሞ ዴሞክራቲክ ግንባር ሊቀመንበር
የተከበሩ ዶር ብርሃኑ ነጋ የግንቦት ሰባት-አርበኞች ሊቀመንበር
የተከበሩ አቶ እያሱ አለማየሁ የኢሕአፓ ሊቀመንበር
የተከበሩ አቶ ስለሺ ጥላሁን የብሄራዊ ሽግግር ምክር ቤት ሊቀመንበር
የተከበሩ አቶ ኦባንግ ሜቶ የአዲስቱ ኢትዮጵያ ሶሊዳሪቲ ንቅናቄ
እንዲሁ የሌሎች ኢትዮጵያዊ ድርጅቶችና እና የሲቪክ ማህበራት መሪዎች

ጤና ይስጥልኝ።

ሸንጎ፣ የሽግግር ምክር ቤት ፣ ግንባት ሰባት ፣ ኦዴፍ እንዲሁም ሶሊዳሪቲ ንቅናቄ ፣ በጋራ ሆነው ቢያንስ ፣ ሌሎች የሰብዓዊ መብት ተሟጋቾችን አካተው፣ በዉጭ ትልቅ የሆነውን የኢትዮጵያዊ ኃይል የሚያባስብ አንድ አማራጭ ኃይል መፍጠር እንዲቻሉ፣ መለስ ዜናዊ ከሞተ ጀምሮ ፣ ጥያቄዎች አቀርብ ነበር። ያኔ መለስ የሞተ ጊዜ በርከት ያሉ ድርጅቶች ተሰባስበው በጋራ አብረዉ እንደሚሰሩ መግለጫ ማውጣታቸውን አስታወሳለሁ። ከዚያ በኋላ ግን ሁሉም ነገር ተረሳ።

አገር ቤት ያሉ ወገኖቻችን በከባድ ሁኔታ ዉስጥ ሆነው የተቻላቸዉን እያደረጉ ነው። በቅንጅት ጊዜ የነበረው እንቅስቃሴ፣ ከዚያ የአንድነት ፓርቲ ሲያደርጋቸው የነበረው የሚሊዮኖች ድምጽ እንቅስቃሴዎች፣ የሰማያዊ ፓርቲና መድረክም በፊናቸው የሚሰሩት ሥራ፣ ስርዓቱን ማስወገድ ባይችልም፣ የሕዝብን ንቃተ ሕሊና በማሳደጉና አገዛዙን እርቃኑ እንዲወጣ በማድረግ አንጻር ከፍተኛ አስተዋጾ አበርክተዋል። አገር ቤት ያሉ ኃይላት፣ ለሕዝቡ ቅርበት ያላቸው እንደመሆኑ፣ ለለወጥ ለሚደረገው ትግል ምንጊዜም ቁልፍና ወሳኝ ሚና የሚኖራቸው ነው የሚሆኑት።

በሌላው መስክ ወያኔን በሚገባው ቋንቋ እናነጋግረዋለን በሚል፣ የትጥቅ ትግል መርጠናል ያሉ ድርጅቶች አሉ። የትጥቅ ትግል የሚደረግ ከሆነ በዋናነት ደጀን (ቤዝ) የሚሆን ጎሮቤት አገር ስለሚያስፈለግ፣ ብቸኛ ያለችው አገር ደግሞ ኤርትራ ስለሆነች፣ ከኤርትራ ጋር መስራት የግድ ነው የሚሆነው። ኤርትራን በተመለከተ የሐሳብ ልዩነቶች ይኖራሉ። ሆኖም ድርጅቶቹ በዚያ በኩል መንቀሳቀስ ያዋጣናል ካሉ ዉሳኔያቸውን በማክበር በዚያ እኩል እንሰራዋለን የሚሉትን ሥራ እንዲሰሩ ብንትወላቸውና ወደ አላስፈላጊ ጭቅጭቅ ባንገባ ጥሩ ይሆናል የሚል እምነት አለኝ።

ይሄ ሆኖም እንደ ግንቦት ሰባት ያሉ ድርጅቶች፣ የትጥቅ ትግል ብቻ ሳይሆን ሌሎች የትግል አይነቶችን እንጠቀማለን የሚሉ እንደመሆናቸው፣ ከትጥቅ ትግሉ ዉጭ ያሉትን ትግሎች በተመለከተ ከሌሎች ጋር በጋራ የማይሰሩበት ምክንያት ሊኖር አይችልም። የትጥቅ ትግል በኤርትራ በኩል ስለሚያደርጉ ደግሞ፣ ሌሎች ከነርሱ ጋር አብረን በጭራሽ አንሰራም የሚል ግትር አቋም መያዝ ያለባቸው አይመስለኝም። ስለዚህ ከሚያለያየን የሚያስማማን ብዙ እንደሆነ በማወቅ፣ በመንስማማባቸው ጉዳዮች በቅንነት ለመሰባሰብ መሞከር አለብን።

አገር ቤት ያሉ ወገኖቻችን ብዙ እየሰሩና ትልቅ ዋጋ እየከፈሉ ያሉ ቢሆንም፣ ሊሰሩትና ሊያደርጉት የማይችሏቸው ተግባራት አሉ። ዉጭ አገር እንዳሉት የአለም አቀፍ ማህበረሰብ በአገዛዙ ላይ ጫና እንዲያደርግ የዲፕሎማሲ ሥራ ሊሰሩ አይችሉም። አገር ቤት ያሉት ሕጋዊ ድርጅቶች ሚስጥራዊ አደረጃጀት በመዘርጋት የእምቢተኝነት ዘመቻዎችን ማድረግ አይችሉም።

ስለዚህ በዉጭ ያለው ኃይል ፣ የአገር ቤት ሰላማዊ ትግሉ በሚቃወም መልኩ ሳይሆን ፣ ኮምፕሊመንት በሚያደረግ መልኩ ፣ ከመቼዉም ጊዜ በላይ ተሰባስቦ፣ አንድ የጋራ ግብረ ኃይል ወይንም አማራጭ ኃይል ፈጠሮ በዉጭ ያለውን ትግል በተቀናጀ መልኩ መምራት ቢቻል ጥሩ ይሆን ነበር።

ሁሉም ድርጅቶች መተባበር እንደሚያስፈልግ ይናግራሉ። ዋናው ችግር ወደ ተግባር ሲመጣ ነው። ለዚህም ደግሞ አንዱ እንቅፋት አለመተማመን ነው። የቅንነት ማነስ ነው።

ከዚህ በፊት ብዙ ተጋጭተን ሊሆን ይችላል። ነገር ግን አንድ ነገር መርሳት የሌለብን ነገር ቢኖር አሁን ወያኔዎች 200% ሕዝባችንን ረግጠው እየገዙ ነው። አላወቅነውም ይሄ የሚያሳየው ሁላችንም መሸነፋችንን ነው። የትጥቅ ትግል እናደርጋለን የሚሉት ነጻ ያወጡትን አንድ ወረዳ የለም። ሌሎቻችን መግለጫዎች ከመደርደርና ስብሰባዎ ከማድረግ ዉጭ የረባ ሥራ አልሰራንም። ሰልፎች ሲደረጉ የሚመጣው ጥቂት ሰው ነው። ፔቲችን ሲደረግ የሚፈርመው ጥቂት ሰው ነው። አንድ ዛሬ ስብሰባ ይጠራል፣ ነገ ሌላው ..እዉነቴን ልንግራችሁ ወያኔዎች ንቀዉናል። ተጋራይ የሚባል አፍቃሪ ህወሃት ፓል ቶክ ክፍል አድሚን የሆነች አንዲት የአገዛዙ ደጋፊ ምን እንዳለች ታወቃላችሁ ? «ዉጭ ያለው ተቃዋሚ ወሬ ብቻ ነው የሚያወቀው። ፈንዲሻ ናቸው።( pop corns ) በባዶ ቡፍ የሚሉ » ነበር ያለችው። ሴትየዋ ተሳስታለች ? መልሱ ለእያንዳንዳችን እተወዋለሁ።

እንግዲህ ቢያንስ ለሸንጎ፣ ለሽግግር ምክር ቤቱ፣ ለግንቦት ሰባት- አርበኞች ፣ ለኦሮሞ ዴሞክራቲክ ግንባር ፣ ለኢሕአፓ ለሶሊዳሪቱ ንቅናቄ እንዲሁም ሌሎች መሳተፍ የሚፈልጉ ድርጅቶች ጥሪ አቀርባለሁ። እነዚህ ድርጅቶች፣ በኢትዮጵያ አንድነት ያምናሉ። የኢሕአዴግ ስርዓት መቀየር አለበት የሚል አቋም አላቸው። ችግሮችና ልዩነቶች በዴሞክራሲ ሊፈቱ እንደሚችሉ ይናገራሉ። ስለዚህ በነዚህ ስስት ነጥቦች ላይ ከተስማሙ ፣ በነዚህ ነጥቦች ዙሪያ የሚሰራ አንድ አማራጭ ኃይል መፍጠር ሊያቅታቸው አይገባም።

አዎን በተለያዩ የፖለቲካ ፕሮግራሞች ዙሪያ ልዩነቶች አሉ። ግን አሁን አንድ ሆነን የምንሰራው አገርን ነጻ ለማውጣትና የዲሞክራሲ ስርዓትን ለመገንባት ነው። ከዚያ በኋላ ሁላችንም በብሄረሰብ ፖለቲካ፣በመሬት ፖሊሲ ..ወዘተረፈ ያለንን ልዩነት ይዘን እርስ በርስ በምርጫ እንፎካከራለን። አሁን ግን መቅደም ባለባቸው ጥያቄዎች ዙሪያ ድርጅቶቹ አንድ ሆነው የማይሰሩበት ምክንያት አይኖርም።

## <u>አማራጭ ኃይሉ ከተቋቋመ በኋላ ምንድን ነው የሚሰራው ?</u>

1. ድርጅቶች ለዉጭ ድርጅቶችንና መንግስታት በተናጥል ደብዳቤዎች መጻፍ የለባቸውም። በተለይም ምእራባዉያን ባለስልጣናት የኛን ደብዳቤዎች የሚያነቡት አይመስለኝም። ለሃያ አመታት የለመዱት ብሶት ብቻ ያካተተ፣ አማራጭ የሌው ደብዳቤዎች ነው በተናጥል የምንልከው።

   ደብዳቤዎቻችን ብስቶ ኬምዘርዘር ባለፈ፣ አማራጮችን አካተው፣ በአንድ ድምጽ በሚጻፉበት ጊዜ ግን ያኔ ሰሚ እናገኛለን። ይህ ይሆን ዘንድ፣ አማራጭ ኃይሉ በአንድ ድምጽ፣ በተጠናና ዉጤት በሚያመጣ መልኩ የዲፕሎማሲ ሥራ ይሰራል። በአንድ ድምጽ ከተናገሩም፣ ተሰሚነታቸውን በእጅጉ ከፍ ያደርገዋልና

2. ኢሳት፣ የኦሮሞ ሜዲያ ኔትዎርክ ፣ ራዲዮዎችን እና ሶሻል ሜዲያዎችን በስፋት በመጥቀም በአገር ቤት የሚደረግ የእምቢተኝነት እንቅስቃሴን ይምራል። አገር ቤት ያሉ ድርጅቶችች ከሕጋዊ ሰላማዊ ትግል ዉጭ ሌላ አይነት እንቅስቃሴ ሊያደርጉ አይችሉም። ይህ በዉጭ ያለው አማራጭ ኃይል ግን፣ በአገር ቤትም ውስጥ ዉስጡን መዋቅር ያላቸው ድርጅቶች ያሉበትን እንደመሆኑ፣ የድርጅቶችን ሥራ ፣ ኮኦርዲኔት የማድረግ ሥራ በመስራት ፣ ሁሉም በጋራ እንዲንቀሳቀሱ ማድረግ ይችላል። ለምሳሌ የኢትዮጵያ ወጣቶች ንቅንቄም ፣ የሽግግር ምክር ቤት፣ ግንቦት ሰባት-አርበኞች፣ ኢሕአፓ .. አገር ቤት ጥንካሬውና ስፋቱ ምን ያህል እንደሆነ ባይታወቅም፣ መዋቅር እንዳላቸው ይናገራሉ። ይህ ግብረ ኃይል እነዚህ ሁሉ አስተባብብሮ በጋራ እንዲንቀሳቀሱ ያደርጋል።

3. በዉጭ የሚደረጉ ሰልፎች፣ ተቃዉሞዎች፣ ፔትሽኖች ..የመሳሰሉ አስፈላጊ ስራዎች አሉ። እነዚህ እስከ አሁን ዉጤት ያላመጡት በተናጥል ስለሚደረጉ ነው። አሁን ግን አማራጭ ኃይሉ ይሆናል እነዚህን እንቅስቃሴዎች የሚመራው። አማራጭ ኃይሉ ጥሪ ሲያቀርብ፣ ሁሉንም ያሳተፈ እንደመሆኑ፣ አንዱ ሜዲያ እያወጣው፣ ሌላው እያፈነው፣ አንዱ ራዲዮ እየተናገረው ሌላ ብሎክ እያደረገው ..አይሆንም። ሁሉም ሜዲያዎች ፣ ሁሉም ራዲዮዎች፣ ሁሉም ቴሌቭዥኖች ይረባረቡበታል። የብዙውዎች ተሳታፊነት ሲኖር ደግሞ የሚደረጉ ሰልፎችና ሌሎች እንቅስቃሴዎች ውጤት ያመጣሉ።

## <u>ይሄንን ማን ያስተባብር ?</u>

በሚወጡ አንዳንድ መረጃዎች ሸንጎ፣ የሽግግር ምክር ቤቱና የኢትዮጵያ ወጣቶች ማህበር አብረው በመስራት ላይ ናቸው። በጋራም መግለጫዎች እያወጡ ነው። ግንቦት ሰባት ከአርበኞች ግንባር ጋር ከመዋሃዱ በፊት በዉይይቶች ይካፈል ነበር። ወደፊት የስብስቡ አካል ይሆናል ተብሎ ይጠበቃል። በአቶ አባንግ ሜቶ የሚመራው የሶሊዳሪቲ ንቅናቄም፣ በዚህ ረገድ ፍቃደኛነት ይኖረዋል የሚል እምነት አለኝ። በመግለጫዎቹ ሶሊዳሪቲ አብሮ መስራት ሁልጊዜ የሚሰብክ እንደመሆኑ። የኦሮሞ ዴሞክራቲክ ግንባርም አብሮ ለመስራት ችግር ይኖረዋል ብዬ አላስብም። ኦዴፍ ሲቋቋም እነ አቶ ሌንጮ ባቲ፣ እነ ዶር በያን የተሰጡትን የተለያዩ ቃል ምልልሶች አድምጫለሁ። የኢትዮጵያ ችግር በዴሞክራሲ ይፈታል የሚል ጠንካራ አቋም ነው ያላቸው።

**እንግዲህ ከአንድ ወር በኋላ ሸንጎ፣ የሽግግር ምክር ቤቱ፣ የኢትዮጵያ ወጣቶች ንቅናቄ እንዲሁም ሌሎች የጋራ ስብስበ ለማዘጋጀት ሐሳብ እንዳላቸው ሰምቻለሁ። ሌሎች ድርጅቶችም ተካተው ፣ በዉጭ ያለን ኢትዮጵያዉያን የሚመራን አንድ አማራጫ ኃይል ብናገኝ ፣ እንዲሁ በባዶ ከመጮህ፣ በተናጥል ዉጤት አልባ እንቅስቃሴ ከማድረግ እንተርፍ ነበር። ፓፐ ኮርን (ፈንዲሻ) መሆናችን ያቆም ነበር።**

ቀደም ሲል እንደገለጽኩት፣ አማራጭ ኃይሉን ለማቋቋም መጻፍና ማውራት ቀላል ነው። ግን ወደ ተግባር ሲኬድ ነው የሚከብደው። ሆኖም በአገራችን ያለው ችግር አስከፊነት ከፊታችን የተደቀኑ መሰናከሎች በቀላሉ፣ በቁርጠኝነትና በፍጥነት እንድናልፍ ያስገድደናል ብዬ አስባለሁ።

ይህ ሂደት በስብሰባና በዉይይት ጊዜ የሚፈጅ ሆኖ ከተገኘ ደግሞ በራሱ አገርን እንደመበደል ነው። ብዙ ጊዜ ስብሰባና ቢሮክራሲ ላይ ጊዜ እናጠፋለን። ብዙ ጊዜ ዉይይት ላይ ጊዜ እናጠፋለን። ሕዝቡ ለትግል ፣ ለሥራ ተዘጋጅቷል። ይህ አማራጭ ኃይል ከሶስት ወራት ባነሰ ጊዜ ዉስጥ ተቋቁሞ መስከረም 1 ቀን 2008 ዓ.ም ከፍተኛ የትግል እንቅስቃሴዎች መደረግ የሚኖርባቸው መሰለኝ። ያ ካልሆነ ግን ህዝቡ ተስፋ ይቆርጣሉ፣ ድርጅቶችን የወረቀት ነብሮች ብቻ ሆነው ይቀራሉ።

ብዙዎቻችሁ እድሜያችሁን፣ ገንዘባችሁን፣ ጉልበታችሁን ለአገርና ለሕዝብ ከስክሳቹሃል። ብዙዎቻችሁ ታስራችሁል፣ ተደብድባቹሃል፣ ደምታቹሃል። ውስጣችሁ የህዝባቹህ ፍቅር ነው ያለው። እርግጠኛ ነኝ ፣ አንድ ላይ በተሎ ተሰባስባችሁ ለሕዝብ ደስታን ለወያኔዎች መርዶን እንደምታበስሩ !!!!

ከታላቅ አክብሮት ጋር

ግርማ ካሳ